

በ: ቴልማ ኤሊጎን-ሮዝ
ምሳሌዎች: ኖዓም ናዳቭ
ተርጓሚ: כנרת
የእድሜ ክልል: መዋዕለ ሕጻናት

שִׂיחָה

በቤትና በመዋእለ ህጻናት "ቋንቋ" ይለያያል
ታሪኩ ልጆችን ካለፈው አስደሳች ጊዜ ጋር እንዲጋለጡ ስለሚያደርጋቸው ስለ ስሜቶችና ሁኔታዎች ከዕለት ተዕለት ሕይወት ጋር እንዲወያዩ ይጋብዛል። ከልጆችዎ ጋር መነጋገርና መጠያየቅ ይችላሉ፡- ባሮን ሮትሺልድ ከመጎበኘቱ በፊት በነበረው ምሽት ሚልካ ለምን ፈራች ለምንስ ታመነታ ነበር? ስላደረገችው ውሳኔ ምን ታስባላችሁ? በመዋእለ ?ህፃናታችሁ ውስጥ ከቤት ውስጥ የተለዩ ህጎች አሉ? ለምሳሌ ምን ምን ደንቦች

חֵקֶר

?በዕብራይሥጥ ምንድን ነው የሚባለው
ሃንቶኽ? ፖስታ? መምህር ዩዲሎቪች ለጓደኛው የላካቸውን ቃላት በመጠቀም ገጹን ደጋግመው ይንብቡ። ቃላቱን ለመጥራትና ወደ ዓረፍተ ነገሮች እንኳን ሳይቀር ለማጣመር ይሞክሩ:- "ሃንቶኹን ልታስተላልፍልኝ ትችላለህ?" እንዲሁም በጋራ ማሰብ ይችላሉ – በየቀኑ ምን ምን ዓይነት የባዕድ ቃላትን እናጣምራለን? የዕብራይሥጥ አቻቸውስ ምንድናቸው? አዲስ የዕብራይሥጥ ቃላትን አንድ ላይ ለመፍጠር መሞከር ይችላሉ።

קְרִיאָה

አህያውን መፈለግ

በእያንዳንዱ ምሥል ላይ የሚገኘውን ግራጫ አህያ አስተውለዋል? በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት ምሥሎች በዝርዝር፣ በቀለምና በፅሁፍ የተሞሉ ናቸው – በገጾቹ መካከል መቆየት፣ ምሥሎችን መመልከት፣ የሚስቡዎትን ነገሮች ማግኘትና ከታሪኩ ጋር የተያያዘውን ትንሽ አህያ መፈለግ ይችላሉ።

שְׁמַע

QR ኮድ

ሚልካ የሚለው ቃል በዕብራይሥጥ እንዴት እንደሚሰማ ማድመጥ ይፈልጋሉ? ኮዱን ስካን ያድርጉና ታሪኩን በፒጃማ ቤተ መፃህፍት ማድመጫ ላይ መስማት ይችላሉ።

הַשְׁרָאָה

ፒንተረስት

[ተጨማሪ ስራዎችን፣ መዝሙሮችንና እንቅስቃሴዎች በፒጃማ ቤተ መጻህፍት ፒንተረስት ላይ]